መልእክት ዘጠኝ

**ግንባታ እና ውጊያ—**
**ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ**
**በመንፈሳዊ ውጊያ የመሳተፍ አስፈላጊነት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፦ ነህ. 4፤ ኤፌ. 1፡19-23፤ 2፡6፣ 21-22፤
4፡16፣ 23-24፤ 6፡10-20

**I. ነህምያ ምዕራፍ 4 የከተማዋን መልሶ መገንባት በተመለከተ የጠላትን ማስተጓጎል ይገልፃል፦**

ሀ. ጠላቶቻቸው ተቆጡ እጅግም ተበሳጩ፤ በአይሁድ ላይ አላገጡ የግንባታ ሥራቸውንም አቃለሉ—ቁ. 1-3፦

1. የግንባታው ሥራ እየጨመረ ስለሄደ ጠላቶቻቸው ተቆጡ፣ መጥተውም ኢየሩሳሌምን በጋራ ለመውጋት አሴሩ—ቁ. 7-8።
2. እግዚአብሔር ስድባቸውን በራሳቸው ላይ እንዲመልስባቸው በመጸለይ ነህምያ በእግዚአብሔር ታመነ፤ ስለዚህ፣ አይሁዶች ለመሥራት ልብ ስለነበራቸው ቅጥሩን ሠሩ—ቁ. 4-6።

ለ. አይሁድም ወደ አምላካቸው ጸለዩ፣ በነህምያም ትእዛዝና መመሪያ ቀንና ሌሊት በጠላት ላይ ጠባቂ አኖሩ፦

1. ታላቁንና የተፈራውን ጌታ እንዲያስቡና ለቤተሰቦቻቸው እንዲዋጉ ባዘዛቸው በነህምያ ማበረታታት በጦር መሣሪያዎች ለመዋጋት ዝግጁ ነበሩ—ቁ. 14።
2. የነህምያ አገልጋዮች እኩሌቶቹ በሥራው ላይ ደከሙ፣ እኩሌቶቹም የጦር መሣሪያዎችን ይዘው ለመዋጋት ተዘጋጁ—ቁ. 16።
3. በአንድ በኩል የእስራኤል ልጆች ሊዋጉ ተዘጋጅተው ነበር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ስለ እነርሱ እንደሚዋጋላቸው በማመን በእግዚአብሔር ታምነው ነበር—ቁ. 9-23።
4. እንደ ዋና አዛዥ ነህምያ ጠላትን ለመዋጋት ከተዘጋጁት መካከል አንዱ ነበር፤ ሌሊት ጥበቃ ላይ ተሳታፊ ነበር፣ እነዚህንም ጉዳዮች ለሌሎች ሳይተው ራሱ ተሳታፊ—ቁ. 17-23።

**II. ቤተ ክርስቲያንን እንደ የእግዚአብሔር ከተማ መገንባት ቀላል ሥራ አይደለም፤ ግንባታ ሊከናወን የሚችለው በመዋጋት ብቻ ነው—ኤፌ. 2፡21-22፤ 4፡16፤ 6፡10-20፦**

ሀ. የእስራኤል ልጆች ከምርኮ በተመለሱ ጊዜ፣ ዕዝራ፣ ነህምያ እና ሌሎች ቤተ መቅደሱንና ቅድስቲቱን ከተማ በጠንካራ ጦርነት መልሶ ለመገንባት ተነሡ።

ለ. ከነህምያ ጋር በግንባታው ላይ ይሠሩ የነበሩ እስራኤላውያን በአንድ እጃቸው ለመገንባት ደከሙ፣ በሌላ እጃቸው ደግሞ ጦርነቱን ለመዋጋት የጦር መሣሪያቸውን ያዙ (ነህ. 4፡17)፤ በእግዚአብሔር ግንባታ ላይ በምንደክምበት ጊዜ ሁሉ ያለጥርጥር በውጊያ እንደምንሳተፍ ይህ ይገልጣል።

ሐ. የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ግንባታን በተመለከተ በእግዚአብሔርና በጠላቱ መካከል እውነተኛ ግጭት፣ ከባድ ውጊያ አለ—ቁ. 1-3፣ 7-8፦

1. ጠላት የእግዚአብሔር ማደሪያ ስፍራ ግንባታ በጥሩ መንገድ ሲሄድ ማየት አይወድም።
2. ሰይጣን ለማቋረጥ፣ ጣልቃ ለመግባት፣ ለማጥቃት እና ለማጥፋት የተቻለውን ሁሉ ያደርጋል—ማቴ. 16፡18-19።

መ. እግዚአብሔር መንግሥቱን እንዲያገኝ ቤተ ክርስቲያንን እንደ መቅደስ መገንባትና ውጊያውን መዋጋት አለብን—6፡10።

ሠ. ቅዱሳን የቤተ ክርስቲያን ሕይወትን ለማሠራጨት ሲፈልሱ፣ ውጊያውን የሚዋጉ ሠራዊት ናቸው—ተዛ. ሐዋ. 8፡4-12።

ረ. ቤተ ክርስቲያንን የሚገነቡ በተመሳሳይ ጊዜ መገንባትና መዋጋት አለባቸው—ነህ. 4፡14፣ 16-21።

ሰ. ያለ ጦርነትና ያለ ውጊያ መንፈስ፣ ግንባታ የለም፤ ግንባታ እጅግ አድካሚ ውጊያን ይጠይቃል።

**III. ለቤተ ክርስቲያን እንደ ክርስቶስ አካል መገንባት፣ የመንፈሳዊ ውጊያ አስፈላጊነት አለ—ኤፌ. 6፡10-20፦**

ሀ. በሚያሳዝን ሁኔታ፣ ዛሬ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከአማኞች መካከል ይህን መንፈሳዊ ጦርነት የሚያውቅ ከሞላ ጎደል የለም ማለት ይቻላል፤ ይህም በሕይወት ከመድከም፣ ከመንፈሳዊ ጥንካሬ እጥረት እና በቂ የሆነ የእውነት ብርሃን አረዳድ ካለመኖሩ የተነሣ ነው።

ለ. መንፈሳዊ ውጊያ በክርስቶስ ድል ላይ የተመሠረተ ነው—ዕብ. 2፡14፤ ቆላ. 2፡15፤ 1 ዮሐ. 3፡8፦

1. የመንፈሳዊ ውጊያ መነሻው ነጥብ በክርስቶስ ድል ላይ መቆም ነው፤ ክርስቶስ ጠላትን እንዳሸነፈ ማየት ነው—መኃ. 4፡8፤ ራእ. 3፡21፤ 5፡5-6፡-
   ሀ. የዲያብሎስን ሥራ እንዲያፈርስ የእግዚአብሔር ልጅ ተገለጠ—1 ዮሐ. 3፡8።
   ለ. ክርስቶስ በተሠግዎው እና በስብዕና ኑሮው በምድረ በዳ በተፈተነበት ጊዜ ሰይጣንን ድል ነሥቶታል—ማቴ. 4፡1-11።
   ሐ. በሞት ላይ ሥልጣን ያለውን ዲያቢሎስን ጌታ ኢየሱስ በሞት ሽሮታል፤ ሰይጣንን ደምስሶ ወደ አለመሆን አምጥቶታል—ዕብ. 2፡14።
2. በምድር ላይ የቤተ ክርስቲያን ሥራ የክርስቶስን ድል ማስጠበቅ ነው፤ ጌታ አስቀድሞ ውጊያውን አሸንፏል፣ ቤተ ክርስቲያንም ድሉን ለማስጠበቅ በዚህ አለች—ኤፌ. 6፡11፣ 13።

ሐ. በቤተ ክርስቲያን እና በሰይጣን መካከል ያለው ውጊያ ጌታን በምንወድና በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ባለን በእኛ እና በሰማያት ባሉት ክፉ ኃይላት መካከል የሚደረግ ውጊያ ነው—ቁ. 12፡-
1. አለቆች፣ ሥልጣናት እና የጨለማው ዓለም ገዢዎች እግዚአብሔር ላይ ባመፀበት ወቅት ሰይጣንን የተከተሉትና በአሁኑ ጊዜ በሰማያት በዓለም አገራት ላይ የሚገዙ ዓመፀኛ መላእክት ናቸው— ቆላ. 1፡13፤ ዳን. 10፡20።
2. ውጊያችን ከሰዎች ጋር ሳይሆን በሰማያት ካሉ ከርኩሳን መናፍስት፣ ከክፉ ኃይላት ጋር መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል።

መ. መንፈሳዊ ውጊያ የክርስቶስ አካል ጉዳይ ነው፤ ውጊያውን በአካሉ ውስጥ መዋጋት አለብን—ኤፌ. 1፡22-23፡-
1. መንፈሳዊ ውጊያ የግለሰብ ጉዳይ አይደለም፤ የአካሉ ጉዳይ ነው—4፡12፣ 16፤ 5፡30።
2. ቤተ ክርስቲያን ብዙዎች የተካተቱባት ተዋጊ ናት፣ አማኞችም በአንድነት ይህች ብዙዎች የተካተቱባትን ተዋጊ ያዋቅራሉ—6፡10-20።
3. ኤፌሶንን ከምዕራፍ 1 እስከ ምዕራፍ 6 ብናነብ፣ ውጊያ የክርስቶስ አካል ጉዳይ እንደሆነ እናያለን፣ አካሉ ደግሞ በክርስቶስ፣ በመንፈስና በሰማያት ያለች አዲስ ፍጥረት ናት—2፡6፡-
   ሀ. የአካሉ ሕይወት ከሌለን በመንፈሳዊ ውጊያ ለመሳተፍ ብቁ አይደለንም።
   ለ. ውጊያውን ለመዋጋት በአካሉ እውነታ ውስጥ መሆን አለብን—4፡12፣ 16።
4. ወደ ሠራዊትነት በጋራ ከተሠራን በኋላ ከእግዚአብሔር ጠላት ጋር መዋጋት እንችላለን—6፡11-12።

ሠ. የእግዚአብሔርን ጠላት ለመዋጋት፣ ክርስቶስን ከሙታን ባስነሣው እና በአየር ላይ ካሉ ርኩሳን መናፍስት ሁሉ በላይ በሰማያት ባስቀመጠው በኃይሉ ታላቅነት የበረታን መሆን አለብን—ቁ. 10፣ 1፡19-22፡-
1. በጌታ መበርታታችን የማስፈለጉ ሃቅ የሚያመለክተው ከሰይጣንና ከክፉ መንግሥቱ ጋር የሚደረገውን መንፈሳዊ ውጊያ በራሳችን መዋጋት እንደማንችል ነው፤ መዋጋት የምንችለው በጌታ እና በኃይሉ ችሎት ብርታት ብቻ ነው—6፡10።
2. የበረታን ስለመሆን የሚናገረው ትእዛዝ ፈቃዳችንን የማንቀሳቀስን አስፈላጊነትን ያመለክታል፤ ለመንፈሳዊ ውጊያ የበረታን ለመሆን ፈቃዳችን ጠንካራና የሚንቀሳቀስ መሆን አለበት—መኃ. 4፡4።

ረ. የመንፈሳዊ ውጊያ መርሆችን ማወቅና መተግበር ያስፈልገናል፡-
1. የመንፈሳዊ ውጊያ የመጀመሪያው መርህ ሥጋዊ የጦር ዕቃዎችን፣ የሰውን ስልቶችን እና ተፈጥሮአዊ ዘዴዎችን መጠቀም አለመቻላችን ነው፤ መንፈሳዊ ጦርነት ከሥጋ ጋር ሳይሆን ከመንፈሳዊ ኃይላት ጋር ስለሆነ (ኤፌ. 6፡12) የጦር ዕቃው ሥጋዊ ሊሆን አይገባም (2 ቆሮ. 10፡3-5)።
2. የመንፈሳዊ ውጊያ ሁለተኛው መርህ የዕርገትን ስፍራ መጠበቅ ነው—ኤፌ. 2፡6፡-
   ሀ. በውጊያ ውስጥ፣ ከጠላት በላይ ያለው ስፍራ ስልታዊ ስፍራ ነው።
   ለ. ሰይጣንና መንፈሳዊ ሠራዊቱ በአየር ላይ ናቸው፤ እኛ ግን ከእነርሱ በላይ በሦስተኛው ሰማይ ተቀምጠናል—ቁ. 6።
   ሐ. ሰይጣንና ሠራዊቱ ከእኛ በታች ናቸው፣ በእኛ መሸነፍም እጣ ፈንታቸው ነው።
3. የመንፈሳዊ ውጊያ ሦስተኛው መርህ መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎችን መጠቀም የሚገባን መሆኑ ነው—2 ቆሮ. 10፡3-5፡-
   ሀ. መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች የጠላትን ምሽጎች ለማፍረስ ብርቱ ናቸው—ቁ. 4-5.
   ለ. በምንዋጋበት ጊዜ፣ በመንፈሳችን ውስጥ ያለውን ስሜት እየነካን፣ እንቅስቃሴዎቻችን ሁሉ በመንፈስ መሆን አለባቸው፣ ይህ እጅጉን መሠረታዊ የሆነ መርህ ነው።

4. የመንፈሳዊ ውጊያ አራተኛው መርህ የውጊያ ጸሎቶችን—የመንፈሳዊ ውጊያ ጸሎቶችን መጸለይ ነው—ማቴ. 6፡9-10፤ 13፦

   ሀ. የቤተ ክርስቲያን ግንባታ ባለበት ጊዜና ቦታ ሁሉ፣ ያንን የሚጻረር የገሃነም ደጆች እንቅስቃሴ አለ፤ ስለዚህ የውጊያ ጸሎቶች አስፈላጊነት አለ—16፡18-19።

   ለ. ከሁሉ የሚበልጥ ታላቅ ዋጋ ያላቸው ጸሎቶች የዕርገት ጸሎቶች መሆናቸውን ካየን፣ ጸሎት ውጊያ መሆኑን መረዳት እንችላለን፣ የውጊያ ጸሎቶችንም እንጸልያለን፤ በኤፌሶን 6 ላይ የተነገረው ጸሎት ባሕሪ እንዲህ ያለ ነው፦

      (1) በሰማያዊው ክልልና ከእግዚአብሔር ዙፋን የተገለጡ ጸሎቶች ሁሉ የውጊያ ጸሎቶች ናቸው—ራእ. 5፡8፤ 8፡3-5።

      (2) በሰማያዊው ክልል ከሆንን፣ የዕርገት ጸሎቶችን፣ የውጊያ ጸሎቶችን መጸለይ እንችላለን—ኤፌ. 2፡6፤ 6፡18።

   ሐ. ስንጠነክር እንታደሳለን፤ ስንታደስ እንሞላለን፤ ስንሞላ ለመዋጋት እንታጠቃለን፤ የመንፈሳዊ ውጊያ ተዋጊ ጸሎቶችን የምንጸልየው በሚዋጋው መንፈስ ነው—3፡14-16፤ 4፡23-24፤ 5፡18፤ 6፡18።

   መ. ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ በሙላት መፈጸም፣ የክርስቶስን አካል ለእግዚአብሔር ክብር እንደ እግዚአብሔር ቤት እና ለእግዚአብሔር መግዛት እንደ እግዚአብሔር መንግሥት ለመገንባት የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ለመልበስ ሁልጊዜ በመንፈስ እየጸለይን፣ በውጊያ ጸሎቶች በአካሉ ውስጥ ውጊያውን በመዋጋት የዲያቢሎስን የተንኮል ዕቅዶች መቃወም ያስፈልገናል—ቁ. 10-20።

© 2022 Living Stream Ministry